**በፌስቡክ፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የቀረበ ሥዕላዊ መግለጫ፡-**

*"መርዓተ አብ!" ወይም፡ "የአብ ሙሽሪት!"*

የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪትና የእግዚአብሔር ልጁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የኾነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ብቅዓቷ፡ የፈጣሪዋ፡ የክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ በአምልኮቱም፡ የእርሱ ተካፋይ ኾናለች::

**ከአቶ ሠመረ ገብረ-መስቀል የቀረበ ጥያቄ፡-**

*በኣምልኮትም የእርሱ ተካፋይ ሁናለች ማለት ምን ማለት ነው??? ኣልገባኝም ኣብራሩልን!*

**ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠ መልስ፡-**

*ይድረስ፡- ለአቶ ሠመረ ገብረ-መስቀል!*

ስለጥያቄዎ፡ እግዚአብሔር ይስጥልን!

ይህን ጥያቄዎን በሚመለከት፡ በጎዋ ሰሌዳችንና በፌስቡክ መድረካችን ላይ ያሠፈርናቸውን አያሌ መልእክቶችና ድርሰቶች፥ የእ-ጦማር ልውውጦችንም፡ እንዴት፡ እስካኹን ሳይመለከቷቸው እንደቀሩ ለማመን ያዳግታል፤ ተመልክተዋቸው ቢኾን ኖሮ፡ ይህን ጥያቄዎን ማቅረብ ባላስፈለገዎ ነበር፤ አኹንም፡ በብርቱ የምናሳስብዎ፡ ከላይ የተጠቀሱትን የጎዋ መዝገቦቻችንን ከፋፍተው፡ እነርሱኑ በማስተዋል እንዲመለከቷቸው ነው።

እስከዚያው ድረስ ግን፡ ከዚህ የሚከተለውን አጭር ማብራሪያ አቅርበንልዎታልና፡ ያንብቡት! ሲያነብቡትም፡ በትክክል ሊገባዎ ይቻልዎ ዘንድ፡ በይበልጥ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ በታነፀው መንፈሳዊ አእምሮዎ ጭምር፡ ተመሥጠው ሊኾን ይገባል። አለዚያ፡ ብዙውን ጊዜ፡ በሓሰት ቍልፍ የመዘጋት፥ በክፋት ጨለማም የመሸፈን ዝንባሌ ያለው ሥጋዊ አንጐልዎ፡ ለብቻው ሊሰማውና ሊረደው፥ ሊያውቀውና ሊቀበለውም አይቻለውምና።

ስለዚህ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ለታነፀው መንፈሳዊ አእምሮዎ፡ የምናብራራው መልሳችን፡ ይኸውልዎ!

**«"የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪትና የእግዚአብሔር ልጁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የኾነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ ብቅዓቷ፡ የፈጣሪዋ፡ የክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ <u>በአምልኮቱም፡</u> የእርሱ ተካፋይ ኾናለች።"** *ማለት፡ ምን ማለት ነው? ኣልገባኝምና፡ ኣብራሩልን!»* ሲሉ ላቀረቡት ጥያቄ፡ መልሱን፡ ራሱ፡ "አልገባኝም!" *ያሉት ዐረፍተ-ነገር፡* መልሱን፡ በግልጽ ሰጥቶዎት ነበር እኮ! ለእርስዎና ምናልባትም፡ እርስዎን ለመሰሉት ኹሉ ጭምር፡ ለምን ሊገባችሁ እንደተቸገራችሁ፡ ለእኛም ሊገባን አልቻለም።

ምክንያቱም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪት፡ [ማለትም፡ሚስት] ከኾነች፥ እናም፡ ኋላ፡ በትስብእት ስሙ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" የተባለው፡ የአንዱ፡ የቀደመው የባሕርየ መለኮት ልጁ፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ እናት ለመኾን ከበቃች፡ የፈጣሪዋ፡ የክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ <u>የአምልኮቱም፡</u> ተካፋይ ከመኾን የሚያግዳት፡ ምንም እንከን ሊኖር እንደማይችል ስለሚታወቅ ነው።

በዚህ ኹሉ፡ ገሃድ እውነታ፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ እውነተኛ ማንነትና ምንነት ለማወቅና ለመገንዘብ ካልቻሉ፡ ባጭር የምንሰጥዎ፡ ተጨማሪ ማብራሪያ፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"አዎን! የእግዚአብሔር አብ፡ አንዲት ሙሽሪት በመኾኗ፡ በመለኮትነት፡ "እግዚአብሔር-ወልድ"፥ በትስብእትነትም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" የተባለው፡ የእግዚአብሔር አንድ ልጁ እናት የኾነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እርሷም፡ እንደእግዚአብሔር አብ፡ 'እግዚአብሔር እም' ተብላ፡ በዚህ ማንነቷ የታወቀችና የታመነባት ስለኾነች፡ <u>ከእርሱ፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር፡ አንድ እግዚአብሔር፣ አንድ አምላክ፥ አንድ ፈጣሪ ናት!"</u>

ይህን እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ አኹንም እንደገና፡ በበለጠ እያፍታታን እናስረዳዎ!

በቅድሚያ ግን፡ ቊም-ነገሩን፡ በቀላሉ ተረድተው፡ ፍሬ-ጉዳዩ፡ በትክክል ይገባዎት ዘንድ፡ ይቅርታ ያድርጉልንና! መጠይቃዊ የኾነ፡ አንድ አስረጅ ኹነታን፡ እስኪ! በምሳሌነት፡ እንዲህ በሚል ቃል እንድናቀርብልዎ ይፍቀዱልን!

እርስዎ፡ ኑሮዎን፡ በጋብቻ መሥርተው፡ ሚስት አግብተውና ልጆችን ወልደው፡ በትዳር ሕይወት የሚገኙ ከኾኑ፡ ልጆቻችሁን ያስገኘው፡ የጾታ ልዩነታችሁ፡ በእኩልነት ደረጃ እንደተጠበቀ ኾኖ፡ በሰብአዊው መብትና ክብር፣ በጠቅላላም፡ በማንነታችሁና በምንነታችሁ ረገድ፡ በማናቸውም ኹኔታ፡ ፍጹም እኩልነት ካልኾነ በቀር፡ የልጆችዎ እናት በኾኑት፡ በባለቤትዎ እና በእርስዎ መካከል፡ "በእርግጥ፡ መበላለጥ አለ!" ብለው ያምናሉ? የሚያምኑ አይመስለንም። በተለይ፡ እርስዎ፡ እውነተኛ አግዓዚ፥ እውነተኛ ዐምሓራ፥ እውነተኛ ክርስቲያን፥ ወይም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ከኾኑ፡ "አዎን! መበላለጥ አለ!" ብለው የሚያምኑ አይመስለንም።

ይህን ተፈጥሮአዊና ሃይማኖታዊ እውነታ መሠረት በማድረግ፡ በተነሣንበት አርእስተ-ነገር ላይ የምናቀርብልዎትን ማብራሪያ፡ በቀላሉ ተረድተው ለመቀበል የሚያዳግትዎ እንደማይኾን እናምናለን።

እንዲህ ከኾነ፡ እግዚአብሔር፡ የጋብቻን ሥርዓት የሠራውና የመሠረተው፡ ለመለኮትነቱ ዘለዓለማዊ ህልውና ሲል፡ ገና፡ በመለኮትነት ባሕርዩ እያለ፥ በሰውነት አግዝፎ ከፈጠራቸው፡ ከአዳምና ከሔዋን ልደት አስቀድሞ መኾኑን ለማወቅና ለመረዳት፥ ለማመንም የሚከብድዎ አይኾንም።

ይህ እግዚአብሔራዊ ዕውቀትና እውነት፥ እምነትና ሥርዓት፡ ከአዳም እና ከሔዋን ልደት፥ ወይም፡ ፍጥረት ጀምሮ፡ "በቅዱሱ ኪዳን፡ የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች" በኾኑት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ዘንድ፡ እነሆ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት፡ በብቸኛ ታማኝነት ተጠብቆ ኖርዋልና።

ይህን መለኮታዊ ምሥጢር፡ ምናልባት እርስዎ፡ እስካኹን ሳያውቁት የቆዩ ከኾኑ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" እያሉ፡ እንዴት ሳያውቁት እንደቆዩ የሚያጠያይቅ ሊኾን ስለሚችል፡ "እንግዴህ ወዲህ፡ ኢትዮጵያዊነትዎን አጽድቀውና አጽንተው ለመቀጠል ከፈለጉ፡ በትክክል ዐውቀውትና አምነውበት ሊኖሩ ይገባዎታል!" እያልን ምክራችንን በመለገሥ፡ ማብራሪያችንን እንቀጥላለን።

"በመጀመሪያ፡ እግዚአብሔር፡ የወንድ፥ ወይም፡ የሴት ጾታነት በሌለው፡ በነጠላ የአካልና የባሕርይ አንድነት፡ ራሱን፡ "እነ=እኔ" በሚል ስም ይኖር ነበር።

ኋላ ግን፡ ዛሬ የምንገኝበትን፡ ይህን የሥነ-ፍጥረት ህልውናና ሕይወት፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር ሊያመጣ፥ ማለትም፡ ፍጥረትን ኹሉ ፈጥሮ፡ እንዲመራለትና እንዲያስተዳድርለት፥ እንዲጠብቅለትና እንዲያኖርለት፡ አንድ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን [ቃልን]፡ በመለኮታዊው አካሉና ባሕርዩ፡ ሊወልድ ፈቃዱ በኾነ ጊዜ፡ ከኹሉ አስቀድሞ ያደረገውን፡ ዕፁብ ድንቅ ሥራ እንመልከት፡-

"እነ=እኔ" በሚል ስም፡ የወንድ፥ ወይም፡ የሴት ጾታነት በሌለው፡ በነጠላ የአካልና የባሕርይ አንድነት፥ መነሻውም በማይታወቅ ጊዜ፡ ይኖርበት የነበረውን፡ ያን እግዚአብሔራዊ አንድነቱን፥ 'እግዚአብሔር አብ' ብሎ፡ በወንድነት ጾታና በወላጅ አባትነት አካልና ባሕርይ፤ እንዲሁም፡ 'እግዚአብሔር እም' ብሎ፡ በሴትነት ጾታና በወላጅ እናትነት አካልና ባሕርይ፡ ያን አንድ ራስነቱን፡ ከኹለት ከፈለ። ከፍሎትም አልቀረ፤ ወደፍጹም አንድነቱ፡ በተዋሕዶ መለሰው።

ልክ፡ ኋላ፡ በአንድ አዳም፡ የተፈጥሮ አካላዊና ባሕርያዊ ብቸኝነት የነበረውን ቀዳሚ የሰውነት አንድነት፡ ሔዋንን፡ ከእዚያ አንድነት ከፍሎ በማስገኘት፡ ባስከተለው ኹለትነትና በመጨረሻ፡ ወደፍጹም አንድነቱ፡ በተዋሕዶ በመመለስ፡ በግዙፉ ሥጋዊ ተፈጥሮ፡ ምሥጢሩን እንደከሠተው ማለት ነው።

አለዚያ፡ በዚህ የመለኮት ተፈጥሮአዊ የጋብቻ ሥርዓት ካልኾነ በቀር፡ እግዚአብሔር አብ፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በመለኮትነት፡ ብቻውን ሊወልደው፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም በመለኮትነት ሊያሠርፀው፡ እንዴት ይቻለው ነበር? አይቻለውም ነበር። በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ እግዚአብሔር እምን ከተዋሓደችው፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ይህንኑ አንድ ልጁን፡ በኢየሱስ መሢሕ ስም፡ በሰውነት እንደወለደው ማለት ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ በመለኮታዊው [የፈጣሪነት] ስሙ፡ "እግዚአብሔር ወልድ"፥ "እግዚአብሔር ቃል"፥ በትስብእት [በሰውነት] ስሙም፡ "ኢየሱስ መሢሕ"፥ "ኢየሱስ ክርስቶስ" የተባለው፡ የዚሁ፡ የአንዱ መለኮታዊ እና ትስብእታዊ ልጃቸው፡ አንድ አባትና አንዲት እናት፡ ታዲያ! እነማናቸው? በጥንታዊ ማንነቱ፡ ጾታ የሌለው፡ ያው አንዱ እግዚአብሔር የኾነውና ኋላ፡ ራሱን ኹለት ያደረገው፡ "'እግዚአብሔር አብ' እና 'እግዚአብሔር እም' ድንግል ማርያም ብቻ ናቸው።

ያ፡ "አነ=እኔ" በሚል ስም፡ የወንድ፥ ወይም፡ የሴት ጾታነት በሌለው፡ በነጠላ የአካልና የባሕርይ አንድነት፡ ይኖርበት የነበረውን፡ ያን እግዚአብሔራዊ አንድነቱን፥ 'እግዚአብሔር አብ' ብሎ፡ በወንድነት ጾታና በወላጅ አባትነት አካልና ባሕርይ፣ እንዲሁም፡ 'እግዚአብሔር እም' ብሎ፡ በሴትነት ጾታና በወላጅ እናትነት አካልና ባሕርይ፡ ያን አንድ ራስነቱን፡ ከኹለት የከፈለበትን፡ ይኼን የአባትነትና የእናትነት አንድነታቸውን፡ "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾኑ!" ባሏቸው፡ በአዳም እና በሔዋን ጊዜ፥ ከእነርሱም በኋላ፡ የወንድ፥ ወይም፡ የሴት ጾታነት በሌለው፡ በብዙው ካዕብነት፡ ራሳቸውን፡ "ንሕነ=እኛ" በሚል ተውላጠ-ስም መግለጣቸውን ማስተዋል ነው።

እምቅድመ ዓለም፡ [ዓለም ከመፈጠሩ በፊት] በመለኮትነቱ፡ ከአብ፡ ያለእናት የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ፡ ድኅረ ዓለም [ዓለም ከተፈጠረ በኋላ]፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ተብሎ፡ ያለአባት፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት ተወለደ!" የሚለው፡ የባዕዳኑ ሃይማኖታዊ ይትበሃል፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖቷ ጸንታ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ለሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት በኖረችው፡ በእግዚአብሔር መንግሥቷ ኢትዮጵያ እና በእኛ፡ በልጆቿ ዘንድ፡ ተቀባይነት የሌለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑ፡ በይፋ ሊታወቅ ይገባል።

ስለዚህ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪትና የእግዚአብሔር ልጁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም መቅደስ ብቻ ሳትኾን፡ መንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ እና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም ስለኾነች፡ "በዚህ ብቅዓቷ፡ የፈጣሪዋ፡ የክብሩ ብቻ ሳይኾን፡ በአምልኮቱም፡ የእርሱ ተካፋይ ኾናለች።" የሚለውን ዘይቤ፡ ይህ፡ እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ የበለጠ አረጋግጦ ያጸናዋል።